በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የአካባቢ፣የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
Environment, Forest and Climate change Commission

ቁጥር 3/9.1/9145/13
Ref. No.
ቀን 29/7/2013
Date

ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ አቃቢ-ህግ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፦- **ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ቁጥር እንዲሰጠው ስለመጠየቅ**

ኮሚሽን መስሪያቤታችን ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒት አያያዝና አወጋገድ ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማስተቸት አስተያየቶችን በማሰባሰብ እና በመስሪያቤታችሁ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት በኮሚሽን መስሪያቤታችን ስራ አመራር አፅድቋል፡፡ በመሆኑም የፀደቀውን መመሪያ የመመሪያ ቁጥር እንዲሰጠው በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

የአካባቢ፣የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን * Environment, Forest & Climate Change Commission

ከሰላምታ ጋር

ፈቃዱ በየነ (ዶ/ር)
ኮሚሽነር

ግልባጭ፣

- ለክብርት የአካባቢ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር
- ለፖሊሲ ህግና ደረጃዎች ዝግጅትና ጥናት ጀነራል ዳይሬክቶሬት

  <u>የአካባቢ የደንና፣የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን</u>

  <u>አዲስ አበባ</u>

☎251-(0)11-170-40 60
251-(0)11-17040 39
✉12760
ቴሌፋክስ
TELE FAX:251-(0)11–170-4158/45
አዲስአበባ፡ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia
Website: www.mefcc.gov.et

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት

# የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

# ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ

2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

## መግቢያ

ደህንነቱ ካልተጠበቀ የእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አወጋገድ ከሚመነጩ የጤና ችግሮች የህብረተሰብን እና የእንስሳት ጤናን እንዲሁም አካባቢን ከብክለት መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የግል ባለሀብቶች ተገቢ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አያያዝ እና አወጋገድ ስርዓት ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማበረታታትና አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አወጋገድ፤ የተቀመጠ የአወጋገድ ስርዓት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

በዚህ መሰረት በአሁኑ ወቅት የሚታየውን ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት የአያያዝ እና የአወጋገድ ሁኔታ ለማሻሻል፤

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1090/2010 በአንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ይህንን ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ አውጥቷል፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Commission Record & Archive

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ቁጥር .11../2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

   1/ **"ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት"** ማለት የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ያለፈበት ወይም የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ባያልፍም በአግባቡ ያልታሸጉ፣ ገላጭ ፅሁፍ የሌላቸዉ፣ የጎደሉ፣ የተሰበሩ እና በአግባቡ ያልተያዙ እና ተመሳስለው የተሰሩ፣ ከጥራት ደረጃ በታች የሆኑ እና ባዕድ ንጥረ ነገሮች የተቀላቀሉባቸው የእንስሳት መድኃኒት ወይም የመድኃኒት ጥሬ ዕቃ ወይም የእንስሳት መድኃኒትን ለመያዝ ያገለገለ ማሸጊያ እቃን ያጠቃልላል፣

   2/ **"በፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ማስወገድ"** ማለት ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት፣ በተገቢ ሁኔታ ከሟሟ ወይም ከተበረዘ እና ከተፈተሸ በኋላ ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ስርአት ሚለቀቅበት መንገድ ነው፣

   3/ **"አደገኛ ንጥረ ነገር"** ማለት በህብረተሰብ እና እንስሳት ጤና፤ በአካባቢ ደህንነት ላይ መርዛማነት ወይም ቁሳዊ ብልሽትን ሊያመጣ የሚችል ንጥረ ነገር ወይም ውህድ ነው፣

   4/ **"የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት"** ማለት የእንስሳት ጤና ምርመራና ህክምና የሚሰጡ የእንስሳት ሆስፒታሎች፣ የእንስሳት ክሊኒኮች፣የእንስሳት ጤና ኬላዎች፣ የምርመራ ማእከላት እና ሌሎች መሰል ተቋማት ናቸው፣

   5/ **"አቅራቢ"** ማለት የእንስሳት መድኃኒት ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያመርት፣ከውጭ አገር የሚያስገባ፣ በጅምላ የሚያከፋፍል ወይም የሚሸጥ ተቋም ነው፣

   6/ **"አስወጋጅ"** ማለት ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት፣ ለማስወገድ ፈቃድ የተሰጠው አስወጋጅ ሰው ነው፡፡

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change
Record & Archive Commission

7/ **"ባለ ከፍተኛ ሙቀት ማቃጠያ"** ማለት ቢያንስ 1200 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በሁለተኛዉ የምድጃ ክፍል ሙቀት ሚያመነጭ ሆኖ የጋዝ ማፅጃ ዕቃ የተገጠመለት ማቃጠያ ነው፣

8/ **"ባለ መካከለኛ ሙቀት ማቃጠያ"** ማለት ቢያንስ 850 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሙቀት ያለው ባለ ሁለት ክፍል ማቃጠያ ምድጃ ነው፤

9/ **"ከፍተኛ የምህንድስና ይዘት ያለው የቆሻሻ ማስወገጃ"** ማለት የጋዝ መምጠጫ፣ የከርሰ ምድር ውሃመከታተያ እንዲሁም የሊቼት ማከሚያ ያለው እና በሰለጠኑ ሰራተኞች ክትትል የሚደረግበት በከፍተኛ ምሕንድስና ዲዛይን የተሰራ ቆሻሻ ማስወገጃ ነው፤

10/ **"የእንስሳት ህክምና መገልገያ"** ማለት ለእንስሳት በሽታ ምርመራም ሆነ ህክምና የሚውል ማንኛውም ቁሳቁስ ማለት ሲሆን፤ ይህም የቁስል መስፊያ ማቴሪያል፣ ሲሪንጅ፣ ፋሻ፣ ጨርቅ፣ ጥጥ ወይም ሌላ ተመሳሳይ እቃ ነው፣

11/ **"ጸረ-ተህዋሲያን"** ማለት በባክቴሪያ፣ በፈንገስ፣ በፕሮቶዞዋ ወይም በሌሎች በሽታ አምጪ ህዋሳት አማካኝነት የሚከሰቱ ኢንፌክሽኖች ለማከም ጥቅም ላይ የሚውል የእንስሳት መድኃኒት ነው፤

12/ **"ጎጂ ባህሪ ለመቀነስ ከሌላ ንጥረ ነገር ጋር በማዋሀድ በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ማስወገድ"** ማለት የእንስሳት መድኃኒትን ከማሸጊያቸው ማለትም ከወረቀት፣ ካርድቦርድ እና ፕላስቲክ ማሸጊያ በመፍታት ከሲሚንቶ፣ ላይም (ኖራ) እና ውሃ ጋር በመደባለቅ ጎጂ ባህሪውን እንዲቀንስ ማድረግ ነው፤

13/ **"በመያዣ በማሸግ ማስወገድ"** ማለት ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት የሚያመጣውን ችግር ለመቀነስ በፕላስቲክ ወይም በብረት በርሜል ውስጥ በማሸግ በተገነባ ግንብ ዉስጥ የሚወገድበት አሰራር ነው።

14/ **"አግባብነት ያለው አካል"** ማለት የእንስሳት መድኃኒት እና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ወይም እንደ ሁኔታው የእንስሳት መድኃኒት እና መኖ አስተዳደር እና ቁጥጥር ተግባራትን በክልል ደረጃ ለማከናወን ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፣

15/ **"አመንጪ"** ማለት ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት የሚያመነጭ ሰው ሲሆን፣ አመንጪው ባልታወቀበት ሁኔታ ጥቅም ላይ የማይውል



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Commission Record & Archive

የእንስሳት መድሃኒት በማወቅ ወይም ባለማወቅ በይዞታው ሥር የተገኘበት ሰው ነው፤

16/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

17/ “ኮሚሽን” ማለት የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ነው፤

18/ “አዋጅ” ማለት የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1090/2010 ነው፤

19/ በወንድ ፆታ የተገለፀው ማንኛውም አገለፃ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒት በህብረተሰብ እና በእንስሳት ላይ ከሚያመጣው የጤና ጠንቅ እና በአካባቢ ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት ለመቀነስ ፤ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የአያያዝ እና አወጋገድ ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር ነዉ፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

1/ ይህ መመሪያ ጥቅም ላይ በማይውል የእንስሳት መድኃኒት አያያዝ እና አወጋገድ ሥራ ላይ በተሰማራ ማንኛውም ሰው ላይ በመላ ሀገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት የሰጡ ሲሪንጆች፣ ቁስል መሸፈኛዎች ጥጥ፣ የቁስል መስፊያ ቁሶች እንዲሁም የአይቪ መያዣያዎች ወይም መሰል ቁሶች እና የራጅ ፊልሞች አወጋገድ በዚህ መመሪያ አልተካተተም፡፡

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

## ክፍል ሁለት

## ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት መለየት፣ ማከማቸት እና ማጓጓዝ

### 5. ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት መለየት

1/ ማንኛውም አመንጪ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ተፈጥሮአዊ ይዘት ላይ መሰረት በማድረግ በአይነታቸው ለይቶ እንዲቀመጡ ማድረግ አለበት፡፡

2/ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች በአይነት የመለየት ስራ በሚከተለው መደብ በመከፋፈል መከናወን አለበት፡፡

ሀ) ጸረ-ተህዋስያን የእንስሳት መድኃኒት፣

ለ) አንቲሴፕቲክ ና እና ዲስኢንፌክታንት፣

ሐ) ጠጣር፣ በከፊል ጠጣር እና በዱቄት መልክ የተዘጋጁ

መ) ፈሳሾች፡- ሶሊዩሽን፣ ሰስፔንሽን፣ አምፑዩልስ እና

ሠ) የታመቀ ጋዝ መያዣ ጣሳዎች ወይም በተቀጣጣይ ንጥረ ነገር የሚገፉ ስፕሬዮች፡፡

3/ እያንዳንዱ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ለማስቀመጥ ራሱን የቻለ ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የእንስሳት መድሃኒት አምራች ወይም አስመጪ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ተለይተው የሚከማቹበት ክፍል ማዘጋጀት አለበት፡፡

5/ ማንኛውም አመንጪ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒቶችን ለመለየት መደበኛ የሆነ የምልከታ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

6/ አግባብ ካለው አካል የሚመደቡ ኢንስፔክተሮች ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒትቶችን በአይነት የመለየት ስራ በአግባቡ መከናወኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

7/ ማንኛውም የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ወይም አስወጋጅ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒትቶችን በአይነት በመለየት ስራው ላይ የሰለጠነ፣ በደህንነት እና አያያዝ ሊመጡ የሚችሉ ችግሮችን በሚገባ የሚረዳ ባለሙያ መመደብ አለባቸዉ፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

8/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት መለየት ስራ በሚከናወንበት ወቅት ሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ መጠቀም አለባቸው፡፡

9/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በአይነት የመለየት ስራ በሚከናወንበት ወቅት በቂ የአየር ዝዉዉር ባለው፣ ደረቅ እና ብርሀን ባለው ቦታ መከናወን አለበት፡፡

10/ ማንኛውም አመንጪ ጥቅም ላይ የማይሉ የእንስሳት መድሃኒቶችን አይነት፣ ብዛት፣ የማሸጊያ አይነት፣ ምርቱ የሚገኝበትን ሁኔታ፣ ጊዜው ያለፈበት ፣ የተጎዳ፣ የተበሳ፣ ያልታሸ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## 6. ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት ማከማቸት

1/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በማከማቸት ስራ ላይ ለመስማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተጠቀሱትን በሟሟላት ከኮሚሽኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2/ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማከማቻ እንዳለው በኮሚሽኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሀ) የህንፃ ዲዛይኑና ግንባታው በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢ ደህንነት ላይ አደጋ የማይስከትል እና ለዚሁ ተግባር ተብሎ የሚዘጋጀውን ደረጃ በሚያሟላ መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፡፡

ለ) ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማከማቻ ስፍራ በቂ ክለላ ወይም አጥር፣ ምልክት እንዲሁም የድንገተኛ ልቀት ወይም ፍሳሽ ቁጥጥር ፋሲሊቲ፤ ፣

ሐ) አዉቶማቲክ የአደጋ ማሳወቂያ/ማስጠንቀቂያ፣ የአደጋ ጊዜ መከላከያ ቁሳቁስ፣ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን እና የእሳት ማጥፊያ፤

መ) ተቀጣጣይ፣ሪአክቲቭ እንዲሁም የማይጣጣሙ አደገኛ ቆሻሻዎች ለየቅል/ለየብቻ መከማቻ

ሠ) ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማከማቻ ስፍራ በቂ የስራ ላይ የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ፣

ረ) የማከማቻ ቦታዉ የተለያዩ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት የሚያደርሱበትን ግፊትና ጉዳት መቋቋሙን እና ለታቀደለት ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ባህሪ ምቹ የሆነ፣



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማከማቸት ስራ ለመሰማራ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሚሟላት አለበት፡፡

ሀ) ማመልከቻ ደብዳቤ ኮሚሽኑ ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት ማቅረብ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማስረጃ ወይም የንግድ ምዝገባ ሠርተፍኬት ማቅረብ፣

ሐ) የማከማቻ ቦታ ያለው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ፣

መ) የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም አመልካቹ ተወካይ ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃና የታደሰ መታወቂያ

ሠ) ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል

ሰ) ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ወይም አክስዮን ወይም ሌሎች የተደራጁ ማህበር ከሆኑ መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደርያ ደንብ በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ

ሸ) የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ እቅድ ማዘጋጀት፣

ቀ) ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማከማቻ በቂ የመድህን ሽፋን፣

በ) በዘርፉ እና በአካባቢ አያያዝ የሰለጠነ ባለሙያ፣

4/ በአይነታቸው የተለዩትን ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች ፣ በደረቅ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ እና ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ መለያ ተደርጎባቸው መከማቸት አለባቸው፡፡

5/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን ለማከማቸት የሚዘጋጅ ክፍል ወይም ቦታ በግልፅ በሚታዩ ፊደላት ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት" ተብሎ በቀይ ቀለም በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ እንዲሁም እንደየአስፈላጊነቱ በሌሎች የሀገሪቱ ቋንቋዎች መጻፍ አለበት፡፡

6/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን የሚያከማች ማንኛውም ሰው ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን ምንነት፣ ይዘትና ባህሪ የሚገልፅ መረጃ ከአመንጪው ወይም ከአጓጓዡ መቀበል መረጃውን በተገቢው ሁኔታ መያዝ አለበት፡፡

7/ ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን ማከማቻ የጉዳት ምርመራ እና የጥንቃቄ ክንዋኔ ኦዲት /Hazard analysis and safety audit/ በተመለከተ ቦታ በየአመቱ የጉዳት ደረጃ ምርመራ በማድረግ ሪፖርት ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change
Record & Archive Commission

8/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ከመንጨበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውጪ ለማከማቸት ወደ ሌላ ከተማ አስተዳደር ወይም ክልል፣ ለማከማቸት ከመጓጓዙ በፊት የከተማ አስተዳደሩን ወይም የክልሉ የይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

7. **ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት ማጓጓዝ**

1/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማጓጓዝ ስራ ላይ ለመስማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተጠቀሱትን በሟሟላት ከኮሚሽኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2/ ቢያንስ የሚከተሉትን መስፈርቶችን የሚያሟላ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማጓጓዥያ እንዳለው በኮሚሽኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሀ) ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ እና ኮንቴኔር የአደገኛ ቆሻሻን ለማጓጓዝ በቂ የሆነና ለዚሁ ተግባር ተብሎ የሚዘጋጀውን ደረጃ የሚያሟላ፤

ለ) በአደገኛ ቆሻሻ አጓጓዝ ቅድመ ጥንቃቄ የሰለጠነ አሽከርካሪ መኖሩ

ሐ) የአደጋ ጊዜ መከላከያ ቁሳቁስ፣ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን እና የእሳት ማጥፊያ ያሟላ ተሽከርካሪ፣

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማጓጓዝ ስራ ለመሰማራ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሟሟላት አለበት፡፡

ሀ) ማመልከቻ ደብዳቤ ኮሚሽኑ ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት ማቅረብ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማስረጃ ወይም የንግድ ምዝገባ ሠርተፍኬት ማቅረብ

ሐ) የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም አመልካቹ ተወካይ ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃና የታደሰ መታወቂያ

መ) ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል

ሠ) ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ወይም አክስዮን ወይም ሌሎች የተደራጁ ማህበር ከሆኑ መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደርያ ደንብ በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ

ረ) የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ እቅድ ማዘጋጀት፣

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

ሰ) ለሚያጓጉዘው ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በቂ የመድህን ሽፋን፣

4/ አጓጓዡ በሚያጓጓዝበት ጊዜ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ምንነት፣ይዘትና ባህሪ የሚገልፅ ሰነዶች መያዝ አለበት

5/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ወደ ታቀደለት ተቋም መድረሱን ማረጋገጥ የሚያሳይ በአጓጓዥ እና በተቀባይ መካከል የጋራ ስምምነት መኖሩን የሚገልፅ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፣

6/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ወደ ጊዜያዊ ማከማቻ ቦታ እና ማስወገጃ በማጓጓዝበት ጊዜ እንዳይሰረቅና ዳግም ጥቅም ላይ እንዳይዉል፣ የመፍሰስ ወይም የመበተን ክስተት እንዳይኖር አጓጓዝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እና ጥበቃ ማድረግ አለበት፡፡

## 8. ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት እንደገና መጠቀምና መልሶ መጠቀም

1/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት በድጋሜ መጠቀም እና መልሶ መጠቀም አይቻልም፡፡

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ውጫው ማሸጊያ ምንም አይነት ንክኪ አለመኖሩን በማረጋገጥ ድጋሜ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል፤ ወይም ድጋሜ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ለሚያውል ሰው ማስተላለፍ አለበት፡፡

3/ ፕላስቲክ፣ ብረት እና የጠርሙስ እቃዎች በድጋሚ ጥቅም ላይ ለማዋል እንደ እቃው አይነትና ድጋሚ እንደምንጠቀመው አገልግሎት ማፅዳት ወይም ዲስኢንፌክቲንግ የመሳሰሉ የማከም ሂደቶች ሊከናወኑ ይገባል፡፡

4/ በማከም ሂደት የሚፈጠርን ቆሻሻ በአግባቡ የመያዝና የማስወገድ ሃላፊነት የአካሚው ይሆናል፡፡

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment, Forest & Climate Change Record & Archive Commission

## 9. ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒት ማከምና ማስወገድ

1/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በማሰወገድ ስራ ላይ ለመስማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተጠቀሱትን በሚሟላት ከኮሚሽኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2/ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማስወገጃ ፋሲሊቲ እንዳለው በኮሚሽኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሀ) ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ተገቢውን ቁሳቁስ፣ መስረተ ልማት፣ ባለሙያና ቴክኖሎጂን ማሟላት፣

ለ) የአደገኛ ቆሻሻን የአደገኛነት ባህሪ፣ ይዘት ለመቀነስ የሚችል፣ መልሶ መጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂን ያለው፣

ሐ) የአደገኛ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል፣ ማከም እና ማስወገድ የሚከናወንበት ቦታ ከማንኛዉም የአየር ብክለት፣ የከርሰ ምድር ዉሃ ብክለት የፀዳ መሆኑን የሚያመላክት ሰነድ ማቅረብ፣

መ) በማከም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ማስወገድ የሚችል ሥርዓት ያዘጋጀ፣

መ) የአደገኛ ቆሻሻን ለማከም የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎችን (ኬሚካላዊ ህክምና/ chemical treatment/ ወይም ፊዚካላዊ ህክምና / physical treatment/ ወይም ስነ-ህይወታዊ ህክምና /biological treatment ወይም እግዳ /immobilization/ ወይም ማጋያት /incineration/ ወይም ወደ ጠጣር ይዘት መቀየር የሚያስችል / solidification/) የሚጠቀም መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማስወገድ ስራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሟሟላት አለበት፡፡

ሀ) ማመልከቻ ደብዳቤ ኮሚሽኑ ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት ማቅረብ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማስረጃ ወይም የንግድ ምዝገባ ሠርተፍኬት ማቅረብ፣



Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

ሐ) የማከማቻ ቦታ ያለው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ፣

መ) የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም አመልካቹ ተወካይ ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃና የታደሰ መታወቂያ

ሠ) ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል

ሰ) ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ወይም አክስዮን ወይም ሌሎች የተደራጁ ማህበር ከሆኑ መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደርያ ደንብ በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ

ሸ) የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ እቅድ ማዘጋጀት፣

ቀ) ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ማስወገጃ በቂ የመድህን ሽፋን፣

በ) በዘርፉ እና በአካባቢ አያያዝ የሰለጠነ ባለሙያ፣

4/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት የሚያስወግድ ሰው የማስወገጃ ቦታዎች ግንባታ የሚያስፈልገው ከሆነ የማስወገጃ ቦታው የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ ማለፍና በሚመለከተው አካል ይሁንታ ማግኘት አለበት፡፡

5/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት የማስወገድ ስራ ላይ የሚሰማራ ሰው የማስወገድ ስራ የሚሰማሩ ሰራተኞች በዘርፉ በቂ ስልጠና ያገኙ መሆን ማረጋገጥ አለበት፡፡

6/ የማስወገድ ስራ ላይ የሚሰማራ ተቋም ሰራተኞች ለማስወገድ ስራ የሚሆኑ በቂ የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ማቅረብና በአግባቡ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

7/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ከመወገዱ በፊት በአስወጋጁ ተቋም በእዝል 2 መሰረት መመዝገብና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

8/ ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አመንጪ የራሱ የማስወገጃ ፋሲሊቲ ከሌለው ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒትን ለማስወገድ ፈቃድ በተሰጣቸው ተቋማት ለማስወገድ ስምምነት መግባት አለበት፡፡

9/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት የማስወገድ ስራ ከተከናወነ በኋላ ለአስወጋጁ፣ ሰለመወገዱ ከአስወጋጅ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለተወገደለት ሰው በአንድ ሳምንት የጊዜ ገደብ ውስጥ መስጠት አለበት፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

10/ በህገወጥ ዝውውር የተገኘ ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ለማስወገድ የአዘዋወሪው ሌሎች ህጋዊ ኃላፊነት እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ ይከናወናል፡፡

11/ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት አወጋገድ ዘዴ፣ መጠንና ሁኔታ በሚደረገው የልየታ እና አወጋገድ ዘዴ መሰረት ይከናወናል፡፡

12/ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን አስወጋጅ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን ለማስወገድ በተረከበ አንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ማስወገድ አለበት፡፡

13/ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን አስወጋጅ ሰው የሙሉ ጊዜ የደህንነት ጥበቃ ሊኖረው ይገባል፡፡

14/በሚቀርቡት የማስወገድ ጥያቄዎች ብዛት ላይ በመመስረት፤ አስወጋጅ ሰው በየሶስት ወሩ ያስወገደውን ቆሻሻአ ዓይነት፣ መጠንና የአወጋገድ ዘዴን ለኮሚሽኑ በሪፖርት ማሳወቅ አለበት፡፡

15/ ኮሚሽኑ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በተሠጠው ይሁንታ መሰረት ስለማስወገዱ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

16/ በማስወገድ ወቅት የተለያዩ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒቶችን በአንድ መያዣ መቀላቀል የለባቸውም፡፡

17/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት ለማስወገድ የተረከበ አስወጋጅ የተረከበውን ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት ካስወገደ በኋላ መድሃኒቱ ተከማችቶበት የነበረበት ቦታን በአግባቡ ያጸዳል፡፡

18/ ማንኛውም አስወጋጅ በማስወገድ ሂደት የሚፈጠርን ቅሪት ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ ያስወግዳል፡፡

19/ በማዘጋጃ ቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ለሚወገድ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒት ከመወገዱ በፊት ከሚመለከተው የማስገጃው አስተዳደር ጋር ስምምነትና ይሁንታን ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡

20/ ማንኛውም አስወገጃ ቆሻሻን ሲያክምና ሲያስወግድ በማንኛውም የአደገኛ ቆሻሻ ስርዓት ከሃገር አቀፍና አለም ዓቀፍ ስምምነት ጋር ተጣጥሞ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

10. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ይዘት</u>

1/ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ያሟላ አመልካች ከሰላሳ የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

2/ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሠጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) የድርጅቱን ሙሉ ስም፤

ለ) ሙሉ አድራሻ፤

ሐ) የተሰማራበት የአደገኛ ቆሻሻ የሥራ መስክ፤

መ) የምስክር ወረቀቱ የተሠጠበት ቀን፤

ሠ) የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ፤

ረ) የባለሙያውን ፎቶ ግራፍ ወይም የድርጅቱን ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ፍቶ ግራፍ

11. <u>የጠፋ ወይም የተበላሸ የምስክር ወረቀትን ስለመተካት</u>

1/ የምስክር ወረቀቱ ዋና ቅጂ ከጠፋ ወይም ከተበላሸ አመልካቹ ለዚሁ ተግባር በኮሚሽኑ የተዘጋጀ ቅፅ ሞልቶ በምትኩ ሌላ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ኮሚሽኑን መጠየቅ ይችላል፤

2/ የጠፋ የምስክር ወረቀትን ለመተካት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር አግባብ ካለው የሕግ አስፈፃሚ አካል ምስክር ወረቀቱ መጥፋቱን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃ መያያዝ አለበት፤

3/ የምስክር ወረቀቱ መጥፋቱ ከተረጋገጠ በምትኩ ሌላ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ሆኖም የተወሰነውን የክፍያ መጠን መፈፀም ይኖርበታል፤

Environment, Forest & Climate Change Commission
Record & Archive

4/ የተበላሸ የምስክር ወረቀት እንዲተካለት የተበላሸውን ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል፤ ሆኖም የተወሰነውን የክፍያ መጠን መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 12. ማመልከቻ ውድቅ ስለማድረግ

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የቀረበ ማመልከቻ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡ ይኸውም አመልካቹ፡-

1/ በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1090/2010 ወይም በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉ መስፈርቶችን የማያሟላ ከሆነ፤

2/ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታ የሌለው ወይም ስራውን መስራት የማይችል መሆኑን ከተወሰነ፤

## 13. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድ

1/ የብቃት ማረጋገጫ የመስክር ወረቀት ሊታገድ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መፈፀማቸውን ሲረጋገጥ ይሆናል፤

ሀ) ቅድመ ሁኔታዎች ወይም መስፈርቶችን አጓድሎ ሲገኝ ወይም የአዋጁንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

ለ) ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር በመጣስ ስራውን ተገቢ ባልሆነ አሠራር ያከናወነ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ለኮሚሽኑ እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ሪፖርቶች ወይም መረጃዎች ሳይቀርቡ ሲቀሩ፤

መ) ፈቃድ ባላገኘበት የአደገኛ ቆሻሻ የሥራ መስክ ተሰማርቶ ከተገኘ

ሠ) በሥራው ሂደት የሥነ ምግባር ጥሰት ወይም ከሙያ አግባብ ውጪ የተፈፀመ ተግባር መኖሩ በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑሥ አንቀፅ 1 መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ሰው ላይ የእገዳ እርምጃው የሚቆየው እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

3/ እገዳው ሊነሳ የሚችለው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱትን ጉድለቶች በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መስተካከላቸው ወይም ሊታረሙ የሚችሉ መሆናቸውን በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ ይሆናል::

4/ የምስክር ወረቀቱን ያሳገዱ ምክንያቶች እገዳው በተጣለ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተስተካከሉ ወይም በሚመለከተው አካል እገዳው እንዳይነሳ ሲወሰን የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል::

14. <u>የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ</u>

1/ የምስክር ወረቀት ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች መሰረት ይሰረዛል፡፡

ሀ) ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በራሱ ጥያቄ ወይም በሌላ ምክንያት ስራውን በራሱ ምክንያት ስራውን አቁሞ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስ

ለ) አመልካቹ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማጭበርበር መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ሐ) የምስክር ወረቀቱ ከህግ አግባብ ውጪ ለሌላ ሰው ተላልፎ ከተገኘ፣

መ) የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው መክሰሩ ወይም መፍረሱ አግባብነት ባለው ፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ወይም

ሠ) አመልካቹ ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ዓላማዎች ጋር የሚቃረኑ ተግባራትን ሲያከናውን መገኘቱ በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ

2/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው የምስክር ወረቀቱን በአስር ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

15. <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ</u>

1/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ለማሳደስ የቀረበ ማመልከቻ በኮሚሽኑ ውድቅ በመደረጉ ወይም የምስክር ወረቀቱ በመሰረዙ ወይም አይታደሰም በመባሉ ወይም በማናቸውም ምክንያት ማመልከቻው ውድቅ በመደረጉ ቅር የተሰኘ አመልካች ሁኔታው በጽሁፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡



Environment, Forest & Climate Change Record & Archive Commission

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቀረበውን ቅሬታ በመመርመር ኮሚሽኑ ውሳኔውን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ያለውን ቅሬታ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ የበላይ ሀላፊ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የኮሚሽኑ የበላይ ሀላፊም የቀረበውን ቅሬታ በመመርመር ውሳኔውን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ የኮሚሽኑ የበላይ ሀላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች ቅሬታውን ለሚመለከተው መደበኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 እና 3 ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ያላቀረበ አመልካች የተወሰነውን ውሳኔ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ቅሬታውን ሊያቀርብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በበቂ ህጋዊ ማስረጃ ከተረጋገጠ ማመልከቻው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

7/ አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ከሰጠው አካል ከፍ ብሎ ለሚገኘው የሥራ ክፍል ኃላፊ ደረጃውን ጠብቆ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

## ክፍል ሶስት

## ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒቶች የአወጋገድ ዘዴዎች

16. ጠጣር፣ በከፊል ጠጣር እና በዱቄት መልክ የተዘጋጀ የእንስሳት መድኃኒት፤

1/ ጠጣር፣ በከፊል ጠጣር እና በዱቄት መልክ የተዘጋጀ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በከፍተኛ ሙቀት በመቃጠል መወገድ አለባቸው፡፡

2/ በተፈጥሮ ይዘታቸው ተሰባብረው ወደ ሌላ ተፈጥሯዊ ይዘት የሚቀየሩና በካይ የማያመነጩ ጠጣር ወይም በከፊል ጠጣር የሆኑ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች፤ በማዘጋጃ ደረቅ ቆሻሻ በሚወገድበት ቦታ ተወግደው፤ 15ሳ.ሜ ውፍረት ባለው ማዘጋጃቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ መሸፈን ይኖርባቸዋል፡፡

3/ ጥቅም ላይ የማይውሉ በጠጣር፣ በከፊል ጠጣር እና በዱቄት መልክ የተዘጋጁ የእንስሳት መድኃኒቶች አወጋገድ የሚከተለውን አሰራር ይከተላል፡፡

ሀ) በጠጣር፣ በከፊል ጠጣር እና በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች ከውጪያዊ ማሸጊያቸው የሚፈቱ ሲሆን ከውስጠኛው ማሸጊያ ሳይፈቱ በንጹህ የፕላስቲክ ወይም የብረት በርሜል ውስጥ መከተት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ማሸጊያቸው የላላ ቦለሶች ወይም ታብሌቶችን ያጠቃላል፡፡

ለ) የውጪያዊው ማሸጊያ መድኃኒት ነክ ወይም ኬሚካል ነክ ካልሆነ ለመልሶ መጠቀም አገልግሎት ይውላል፡፡

ሐ) ቦለስ ወይም ታብሌቶች በፕላስቲክ ወይም በፎይል ማሸጊያዎች ከታሸጉ ከውጪያዊ ማሸጊያቸው መውጣት ወይም መፈታት ሲኖርባቸው ከውስጠኛው ማሸጊያ ግን አይፈቱም፡፡

መ) በብልቃጥ ወይም በሳቸት የታሸጉ ጥቅም ላይ የማይውሉ ዱቄት የእንስሳት መድኃኒቶች ከዉጫዊ ማሸጊያቸው መፈታት ሲኖርባቸዉ ነገር ግን ከብልቃጡ ወይም ከሳቸቱ መውጣት የለባቸውም፡፡

ሠ) ማሸጊያቸው የላላ ቦለሶች ወይም ታብሌቶች ከሌሎች ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች ጋር በብረት በርሜሎች ውስጥ ተቀላቅለው መቀመጥ ይችላሉ፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment, Forest & Climate Change Commission Record & Archive

17. ጥቅም ላይ የማይውል ፈሳሽ የእንስሳት መድኃኒት፤

1/ ፈሳሽ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ከሲሚንቶ ጋር አሸጎ (በመደባለቅ)፣ በከፍተኛ ሙቀት በማቃጠል ወይም በሲሚንቶ ማቃጠያ ምድጃ በማቃጠል ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

2/ ፈሳሽ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒት በተፈጥሮ ይዘታቸውን ወደ ሌላ ተፈጥሮአዊ ንጥረ ነገር መቀየር የሚችሉና በካይ የማያመነጩ እንደ ቫይታሚኖች እና በደም ስር የሚሰጡ መድሃኒቶች በፈሳሾች በውሀ እንዲቀጥኑ ተደርገው በፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

3/ የተለያየ የጥንካሬ ይዘት ያላቸው ጎጂ ያልሆኑ ውህዶች፣ ጨው፣ አሚኖ አሲድ፣ ሊፒድ ወይም ግሉኮስ በፍሳሽ መስመር ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

4/ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፈሳሽ የእንስሳት መድኃኒት በሌላ ፈሳሽ ተበርዞም ሆነ ሳይበረዝ በገጸ ምድር ውሀ ላይ ማስወገድ ክልክል ነው፡፡

18. ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት አምፒዩልስ (Ampoules)

1/ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒት ለማስወገድ አምፒዩልስ በጠንካራና በማያሰርግ የብረት በርሜል ወይም ባልዲ ውስጥ መፈጨት አለባቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) የተፈጨው አምፒዩልስ ለስለታማ ቁሶች ተብሎ በተዘጋጀ መያዣ ውስጥ ከታሸገ በኋላ ማዘጋጃቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መወገድ አለበት፡፡

ለ) ከአምፒዩልስ የሚወጣው ፈሳሽ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ፈሳሽ የእንስሳት መድሃኒት በሚወገድበት አግባብ ይወገዳል፡፡

3/ ጸረ-ተህዋስያን ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒትን የያዘ አምፒዩልስ በመፈጨት ፈሳሻቸውም ወደ ፍሳሽ መስመር በመልቀቅ አይወገዱም፡፡ ይሁን እንጂ በፕላስቲክ ወይም ብረት መያዣ በማሸግ ወይም ጎጂ ባህሪያቸውን በመቀየር ማስወገድ ይቻላል፡፡

4/ አምፒዩልስ በማቃጠል ወይም በከፍተኛ ሙቀት ማቃጠያ በማቃጠል ማስወገድ ክልክል ነው፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment, Forest & Climate Change Commission Record & Archive

19. **ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት የያዙ ብልቃጦች** (vials)

1/ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒት ብልቃጦች ለማስወገድ በጠንካራና በማያሰርግ የብረት በርሜል ወይም ባልዲ ውስጥ መፈጨት አለባቸው፡፡

2/ በዚህ. አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) የተፈጨው ብልቃጦች ለስለታማ ቁሶች ተብሎ በተዘጋጀ መያዣ ውስጥ ከታሸገ በኋላ ማዘጋጃቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መወገድ አለበት፡፡

ለ) ከብልቃጡ የሚወጣው ፈሳሽ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ፈሳሽ የእንስሳት መድሃኒት በሚወገድበት አግባብ ይወገዳል፡፡

3/ ጸረ-ተህዋስያን የያዙ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒትን ብልቃጦች፤ መፈጨት የሌለባቸም፡፡

4/ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒትን ብልቃጦች የሚገኙ ፈሳሻቸውም ወደ ፍሳሽ መስመር በመጨመር አይወገድም፡፡

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጸረ-ተህዋስያን የያዙ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒትን ብልቃጦች በፕላስቲክ ወይም በብረት መያዣ በማሸግ ወይም ጎጂ ባህሪያቸውን በመቀየር ማስወገድ ይቻላል፡፡

20. **ጥቅም ላይ የማይውል ጸረ- ተህዋስያን የእንስሳት መድኃኒት** (Anti-infectives)

1/ ጸረ-ተህዋስያን የእንስሳት መድኃኒቶች በከፍተኛ ሙቀት በማቃጠል ዘዴ መወገድ ያለባቸው

2/ ጸረ-ተህዋስያን የእንስሳት መድኃኒቶች ሳይታከሙ መወገድ የለባቸውም፡፡

21. **ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት ክትባቶች** (Vaccines)

1/ ጥቅም የማይውሉ የእንስሳት ክትባት መድኃኒቶች ከመወደዳቸው በፊት የአደገኛ ባህሪያቸዉ ለመቀነስ መታከም አለባቸው፡፡ ይህም በሚከተለው መንገድ ሊከናወን ይችላል፡፡

ሀ) በአዉቶክሌቭ (Authoclave) ዉስጥ በ121-134ዲግሪ ሴንትግሬድ ለ15 ደቂቃ በእንፋሎት መቀቀል ወይም በ55 ዲግሪ ሴንትግሬድ በፈላ ዉሃ ዉስጥ ለ30 ደቂቃ መቀቀል ወይም በ95ዲግሪ ሴንትግሬድ ለ30 ሴኮንድ መቀቀል፤

ለ) ክሎሪን፣ በረኪና፣ ፎርማሊን ወይም አልኮል በመሳሰሉ ኬሚካሎች



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Commission Record & Archive

2/ የክትባት መድኃኒቶች አደገኛ ባህሪያቸዉ ከቀነሰ በኋላ በከፍተኛ ሙቀት ማቃጠያ ይወገዳሉ፡፡

22. **ጥቅም ላይ የማይውል ዲስኢንፌክታንቶች** (Disinfectants)

1/ ጥቅም ላይ የማይውሉ ዲስኢንፍክታንቶችን ለማስወገድ ቅድሚያ መበረዝ ሲኖርበት የተበረዙ ዲስኢንፌክታንቶች አግባብ ባለዉ ተቆጣጣሪ አካል ክትትል በፍሳሽ ማስወገጃ መስመር በሙሉ ቀን በተለያየ ሰዓት አማካይነት 50 ሊትር መብለጥ የለበትም፡፡

2/ ዲስኢፌንታንት በገጸ ምድር ውሀ ላይ ማስወገድ ክልክል ነው፡፡

23. **ጥቅም ላይ የማይውል የላብራቶሪ ሪጀንቶች**

1/ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ከመወገዳቸው በፊት ጠጣር እና ፈሳሽ ኬሚካል ቆሻሻ ተለይተው መለያ ተደርጎባቸው መከማቸት አለባቸው፡፡

2/ ሁሉም የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች አደገኛ ኬሚካሎች ተገቢ በሆነ እና ለኬሚካላዊ ይዘታቸው ተስማሚ በሆነ መያዣዎች ታሽገው መያዝ አለባቸው፡፡

3/ የፈሳሽ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ኬሚካል ቆሻሻ መያዣዎች ሙሉ በሙሉ መሞላት የሌለባቸው ሲሆን ከ5-10 በመቶ የመስፋፊያ ክፍት ቦታ ሊኖር ይገባል፡፡

4/ ባገለገሉት መያዣዎች ቆሻሻ ከመሰብሰቡ በፊት መያዣዎቹ ከሚሰበሰበው ቆሻሻ ጋር የንጥረ ነገር ውህደት በመፍጠር አደጋ እንዳያስከትሉ በሚገባ መታጠብ እና መለቅለቅ አለባቸው፡፡

5/ በውሀ የተበረዙ አሲዶች ወይም ቤዞች (ከከባድ ብረት እና ከሀሎጅን ነጻ የሆኑ) በኒውትራላይዜሽን ማጠራቀሚያዎች የአሲድነት መጠናቸው (ፒኤች) በ6 እና በ9 መካከል እንዲሆን ከተስተካከለ በኋላ ወደ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ከፍተኛ መጠን ባለው ውሀ መለቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

6/ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ኬሚካል ቆሻሻ በፍሳሽ ማስወገጃ መስመር መወገድ የሌለባቸዉ፡፡

ሀ) ተቀጣጣይ (የሚቀጣጠሉበት የሙቀት መጠን ከ187 ዲግሪ ፋራናይት ወይም 86 ዲግሪ ሰንትግሬድ በታች የሆኑ ወይም ለዉጥ የሚያመጡ (ሪአክቲቭ) ኬሚካሎች፣

ለ) ከፍተኛ የአሲድነት ወይም የቤዝነት መጠን ያላቸው ኬሚካሎች፣



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change Record & Archive Commission

ሐ) መርዛማ የሆኑ ከባድ ብረት፣ ካንሰር የሚያመጡ፣ የዘረመል ተጽዕኖ ያላቸዉ እና የፅንስ እድገት ላይ እክል የሚፈጥሩ ኒውትራላይዝ ያልተደረጉ ወይም ያልተገሩ ኬሚካሎች፣

መ) ሬዲዮአክቲቭ ዝቃጮች ፣

ሠ) ምንነታቸው ያልታወቁ ወይም ያልተለዩ ኬሚካሎች፣ ወይም ጠጣር ንጥረ ነገሮች በውሀ የማይሟሙ ንጥረ ነገሮች እና እንደ ቅባት እና ዘይት የመሳሰሉ ንጥረ ነገሮች፣

ረ) ከፍተኛ ጥንካሬ ያላቸዉ የማቅለሚያ ውህዶች፣

24. **ሌሎች ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት ኬሚካሎች አወጋገድ ዘዴዎች**

1/ በተፈጥሮ የሚገኙ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት ኬሚካሎች 25 ሊትር ወይም ከዚያ በታች በቀን በሆነ መጠን ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ይወገዳሉ፡፡ ይህም የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል

ሀ) አሲቴትስ፡ Na, K, Ca, እና $NH_4$፣

ለ) አልኮል፡ በውሀ የሚሟሟ እና ወደ 10 በመቶ ወይም ከዚያ በታች መጠን የተበረዘ፣

ሐ) አሚኖ አሲዶች እና የሚፈጥሩት ጨው፣

መ) ሲትሪክ አሲድ እና የ Na, K, Mg, Ca, $NH_4$ ጨው፣

ሠ) ኢታይሊንግ ግላይኮል፡ ወደ 10 በመቶ ወይም ከዚያ በታች የተበረዘ፣

ረ) ላክቲክ አሲድ እና የNa, K, Mg, Ca, NH4 ጨው፣

ሰ) የስኳር አይነቶች ፡ ዴክስትሮስ፣ ፍሩክቶስ፣ ግሉኮስ፣ ሱክሮስ፣

2/ ኦርጋኒክ ያልሆኑ ጥቅም ላይ የማይውል የኬሚካል ቆሻሻዎች መጠናቸው 25 ሊትር ወይም ከዚያ በታች በቀን በሆነ መጠን ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ይወገዳሉ፡፡ ይህም የሚተሉትን ሊያጠቃልላል ይችላል፡፡

ሀ) መደበኛ የብረት ንጥረ ነገር ያልያዙ አሲዶችና እና ቤዞች፡ ኒውትራላይዝድ ፒኤች (6-9) ያላቸው፣

ለ) ባይካርቦኔት፡- Na, K,

ሐ) ብሮማይድ፡- Na, K,

መ) ካርቦኔት፡- Na, K, Mg, Ca

ሠ) ክሎራይድ፡- Na, K, Mg, Ca



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Commission

ረ) አዮዳይድስ፡- Na, K

ሰ) ፎስፌት፡- Na, K, Mg, Ca እና NH4

ሸ) ሳልፌት፡- Na, K, Mg, Ca እና NH4

3/ ሀሎጂኔትድ የሆኑ አሟሚዎችና መርዛማ የሆኑ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት ፈሳሽ መድሃኒቶች በሲሚንቶ ማቃጠያ ምድጃ ውስጥ በማቃጠል ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

4/ ውሃ አዘል የብረት ውህዶች ከመወገዳቸው በፊት የብረት ይዘታቸው ከውስጣቸው መውጣት አለበት፡፡

5/ ኦርጋኒክ የሆኑ ውህዶች በማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ማስወገድ ክልክል ነው፡፡

6/ ጠጣር የኬሚካል ቆሻሻዎች እና የማይዋሃዱ አሟሚዎች (ሶልቨንትስ) በፕላስቲክ ወይም በፋይበር በርሜል ተከተው በከፍተኛ ሙቀት በማቃጠል ይወገዳሉ፡፡

26. **ሌሎች ጥቅም ላይ የማይወሉ የእንስሳት ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ማስወገድ፤**

1/ የፕላስቲክ ስሪንጆች ከመርፌያቸው ከተለዩ በኋላ ፕላስቲክ ቆሻሻን መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ መልሶ መጠቀም ስራ ላይ ይውላሉ፡፡

2/ በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሲሪንጅ የተለዩ መርፌዎች በከፍተኛ ሙቀት በማቃጠል ይወገዳሉ፡፡

3/ ጥቅም ላይ የማይውሉ ያልተበከሉ የቁስል መሸፈኛ ፋሻ፣ ጥጥ፣ የመስፊያ ቁሳቁሶች እንዲሁም በደም ስር መድኃኒት መስጫ እቃዎች ቆሻሻ በማዘጋጃ ቤት ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

27. <u>**አግባብነት ያለው አካል ተግባርና ሃላፊት**</u>

1/ የእንስት መድሃኒት አያያዝ ክትትልና ቁጥጥር ሲያደርግ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒት አያያዝ ሁኔታን ይከታተላል፣ ህግን ተላልፈው በተገኙት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

2/ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ከሚውሉ ተለይተው መለያ ተደርጎባቸው፣ በመዝገብ ስለመያዛቸው፣ በአግባቡ ስለመከማቸታቸው፣ ተጓጉዘው፣ በአግባቡ ስለመወገዳቸው ከኮሚሽኑ ጋር በጋራ ክትትል ያደርጋል።



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Commission Record & Archive

3/ አመንጪዎች በይዞታቸው ስር የሚገኝን ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድሃኒቶችን አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ እንዲይዙና እንዲያስወግዱ ድጋፍ ያደርጋል፣ ፣ የግንዛቤ ማሳደጊያ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፡፡

4/ ህግን በተላለፉት ላይ ከኮሚሽኑ ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

5/ የባለድርሻ አካላትን በእንስሳት መድሃኒት አያያዝ ላይ ተሳትፎቸውን ያሳድጋል፣ በጋራ ይሰራል፤

6/ እንደ አስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ከኮሚሽኑ ጋር በመሆን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

7/ አመንጪዎች ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድሃኒት እንዲቀንሱ ስርዓቶቶችን መዘርጋታቸውን ያረጋገጣል፡፡

8/ ህገወጥ ጥቅም ላይ የማውል የእንስሳት መድሃኒት በሚቆጣጠራቸው ተቋማት ላይ ያለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Record & Archive Commission

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

28. **ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጣረስ ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

29. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ እንደገና ማሻሻል ይችላል፡፡

30. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ.......................ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አባበ፣ ኢትዮጵያ

ፈቃዱ በየነ (ፕ/ር)

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

ኮሚሽነር



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Commission Record Archive

# ዕዝል 1
# የአወጋገድ ዘዴዎች ወይም መንገዶች

**1. ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ለአቅራቢው ወይም ለአምራቹ ወይም ለለጋሽ ድርጅቱ ስለመመለስ**

በሀገር ውስጥ ለማስወገድ አስቸጋሪ የሆነ ወይም በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር የገባ የእንስሳት መድኃኒት በአግባቡ እንዲወገድ ወደ መጣበት ወይም ተመረተበት ሀገር የመመለስ ሃላፊነት የአቅራቢው ወይም የአምራቹ ይሆናል፡፡

**2. ቁጥጥር በሚደረግበት የምህንድስና ይዘት በሌለው የማስወገጃ ቦታ የሚከተሉት ኀጂ ወይም አደገኛ ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች መወገድ የለባቸውም:-**

ሀ/ አደገኛ/ኀጂ ፈሳሽ እና አደገኛ/ኀጂ ፈሳሾችን በውስጣቸው የያዙ ማቴሪያሎች፣

ለ/ ከፍተኛ የመትነንና የመቀጣጠል ባህሪ ያለው ፈሳሽ፣

ሐ/ ጉልህ የሚኔራል ይዘት ያለው ፈሳሽ፣

መ/ በድንገት የሚቀጣጠል ጠጣር፣

ሠ/ ጠንካራ አክስዳይዚንግ ወይም ሪዱዩሲንግ ባህሪ ያላቸው፣

ረ/ በቀላሉ ሊፈነዱ የሚችሉ፣

ሰ/ የታመቁ ጋዞች፣

ቀ/ በከፍተኛ ሁኔታ የኬሚካል ለውጥ ወይም ውህደት የሚፈጥሩ፣

በ/ በውሃ ሲሟሙ ባህሪያቸውን የማይለውጡ ማቴሪያሎች፣

ተ/ የኦርጋኖ-ሀሎጅን ዉህዶች፣

ቸ/ጉልህ መርዛማነት ያላቸው የሚተኑ ማቴሪያሎች፣

ኀ/ ከዉሃ፣ ከአየር፣ ከተበረዘ አሲድና ቤዝ ጋር ሲዋሃዱ አደገኛ ጋዝ ወይም አደገኛ አፀ-ግብሮት ወይም ሪአክሽን የሚፈጥሩ ንጥረ-ነገሮች፣

ነ/ ከፍተኛ ሀይል ያለዉ ወይም ያልተበረዘ አሲድና ቤዝ፣

ኘ/ ባዶ መያዣዎች ካልተሰባበሩ ወይም ካልደቀቁ በስተቀር፣

አ/ ምናልባት ማሸግ ወይም ኀጂ ባህሪውን መቀነስ ካልተቻለ ቁጥጥር በሚደረግበት የምህንድስና ይዘት በሌለዉ የማስወገጃ ቦታ 15 ሴ.ሜ ዉፍረት ባለዉ መደበኛ ቆሻሻ በመሸፈን ማስወገድ ይቻላል፡፡

**3. ከፍተኛ የምህንድስና ይዘት ያለው የቆሻሻ ማስወገጃ** (Highly Engineered Sanitary Landfill) **ሊያሟላቸው የሚገባ መስፈርቶች፤**

1/ በከፍተኛ ምህንድስና የሚዘጋጁ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች መረጣ፣ ዲዛይንና አሰራር ከአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ጋር ተስማሚ መሆን አለበት፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Commission Record & ... Commission

2/ በከፍተኛ ምህንድስና የሚገነቡ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች አካባቢን፣ የከርሰ ምድር ዉሃን፣ ወንዞችንና አየርን ከብክለት የሚጠብቅ መሆን አለበት።

3/ በከፍተኛ ምህንድስና የሚዘጋጁ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ውሃ ከሚፈስባቸው ቦታዎች 150 ሜትር የሚርቅ የተቆፈረ ጉድጓድ ሊኖራቸው ይገባል።

4/ በከፍተኛ ምህንድስና የሚዘጋጁ ማስወገጃ ቦታዎች ጋዝ ወደ አየር እንዲሁም የውሃ ሊቼት ወደ አካባቢ እንዳያልፍ በሚገድቡ ማቴሪያሎች መታሸግ እና መዘጋት አለባቸው።

5/ በከፍተኛ ምህንድስና የሚዘጋጅ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ፤ የጋዝ መምጠጫ ክፍል እንዲሁም የከርሰ ምድር ውሃ ሁኔታ መከታተያ እና የውሃ ሊቼት ማከሚያ ክፍል ተያይዞ ሊገነባለት ይገባል።

6/ የጋዝ መምጠጪያ ወይም መሳቢያ ክፍሉ የተሰበሰበውን ጋዝ እንዲያቃጥል ወይም ወደ ሀይል እንዲቀይር ተደርጎ መሰራት አለበት።

7/ የጽዳት ሁኔታን ለመጠበቅ በየእለቱ የሚወገድን ጠጣር ቆሻሻ እንዲጠቀጠቅ ተደርጎ በአሸዋ እና በአፈር መሸፈን አለበት።

4. **በመያዣ በማሸግ በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ማስወገድ** (Landfill by Waste Immobilization; Encapsulation)

1/ ከብረት ወይም ፕላስቲክ የተሰሩ ንጹህ መያዣዎች ለዚህ አይነት የማስወገድ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን ተቀጣጣይ ወይም አደገኛ ማቴሪያሎችን ለማሸግ ጥቅም ላይ ውለው የነበሩ በርሜሎችን መጠቀም የተከለከለ ነው።

2/ በርሜሎች ከሚይዙት አቅም 65 በመቶ በጠጣር ወይም በከፊል ጠጣር ከውጨኛው ማሸጊያ (secodary pakage) የወጣ በመጀመሪያው ማሸጊያ (primary pakage) ውስጥ ያለ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት መሞላት ያለበት ሲሆን ቀሪው ክፍል እንደ ሲሚንቶ፣ የሲሚንቶ እና ኖራ ወይም ላይም ውህድ፣ ፕላስቲክ ፎም ወይም አሸዋ መሞላት አለበት።

3/ በበርሜሎች ውስጥ የሚሞላው የኖራ ወይም ላይም፣ ሲሚንቶ እና ውሀ ውህድ ንጽጽር 15፣15፣5 በክብደት መሆን አለበት።

4/ በርሜሎች ክዳናቸው ከታሸገ ወይም ከተበየደ በኋላ በርሜሎቹ በማስወገጃ ቦታው የታችኛው ክፍል እንዲቀመጡ ተድርጎ ወደ ቦታው በሚመጣ አዲስ መደበኛ ጠጣር ቆሻሻ መሸፈን አለበት።

5. **ጎጂ ባህሪን ለመቀነስ ከሌላ ንጥረነገር ጋር በማዋሀድ በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ማስወገድ** (Landfill by Waste Immobilization: Inertization)፤

1/ ለዚህ ስራ ግራይንደር ወይም ሮለር፣ ኮንክሪት ማዋሀጃ እንዲሁም ሲሚንቶ፣ ኖራ እና ውሀ ያስፈልጋሉ።

2/ ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት በሚወገድበት ጊዜ ከታሸገበት የፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ካርድ ቦርድ መለየት አለበት።



የአካባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Commission Record

3/ ጥቅም ላይ የማይውለው የእንስሳት መድኃኒት በአንድ ላይ ተፈጭቶ ከውሃ፣ ሲሚንቶ እና ላይምጋር በማዋሀድ፤በንጽጽር ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት 65%፣ ላይም 15% ፣ሲሚንቶ 15%፣ ዉሃ 5% ወይም ከዚያ በላይ በያዘ ውህድ እንዲደባለቁ ይደርጋል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ውህዱ በፈሳሽ ይዘቱ በኮንክሪት ሚክሰር አማካኝነት ወደ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ተጓጉዞ እንደ መደበኛ ቆሻሻ በመጣል እንዲበተን ይደረጋል፡፡

## 6. በፍሳሽ ቆሻሻ መስመር መልቀቅ (Flushing into Sewer)

1/ ወደ ፈሳሽ ቆሻሻ መስመሮች ከመለቀቁ በፊት ፈሳሽ የእንስሳት መድኃኒቱ ኒውትራል ይዘት እንዲኖረው አስፈላጊውን የማቅጠን ወይም የመበረዝ ስራ እንዲሁም የፒኤች ይዞታው ከ6 እስከ 9 መሆኑ ለመከታተል፤ ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ጉድጓድ ውስጥ መከናወን አለበት፡፡

2/ የመበረዝ እና ወደ ፈሳሽ መስመር የመልቀቅ ስራ የሚከናወነዉ አግባብ ባለዉ አካል በተመደቡ ኢንስፔክተሮች ቁጥጥር አማካኝነት መሆን አለበት፡፡

3/ የተበረዙ ፈሳሾች፣ በደምስር የሚሰጡ ፈሳሽ መድኃኒት እንዲሁም ከ50 ሊትር ያልበለጡ የተበረዙ ዲስኢንፌክታንቶች ወደ ፈሳሽ ማስወገጃ መስመር የሚለቀቁ ይሆናል፡፡

4/ ፈሳሽ ጸረ-ተህዋስያን የእንስሳት መድኃኒት አወጋገድ በተመለከተ አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 3ን ይመልከቱ፡፡

5/ በፍሳሽ ቆሻሻ መስመር የሚፈጸም አወጋገድ በአካባቢ፣ በህብረተሰብ እና በእንስሳት ጤና ላይ ተጽእኖ እንዳይፈጥር ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

6/ ያልተበረዙ ዲስኢንፌክታንቶችን እና አንቲሴፕቲኮችን ወደ ፍሳሽ መስመር መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡

## 7. ባለ መካከለኛ ሙቀት ማቃጠያ (Medium-Temperature Incineration)

1/ ባለ መካከለኛ ሙቀት ማቃጠያ ምድጃዎች ባለጥንድ ክፍል ወይም የመቀጣጠያ ጊዜ ቆይታው በሁለተኛ የምድጃ ክፍል ቢያንስ 2 ሰከንድ በሆነና መካከለኛ በሆነ የመቀጣጠል ሂደት ከ 850-1000 ዲግሪ ስንትግሬድ ፓይሮሊቲክ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፡፡

2/ ማቃጠያ ምድጃዎች በሚመለከተው አካል ልኬታቸው መፈተሽ ያለበት ሲሆን፤ ጥያቄ ሲቀርብም አግባብ ላለው አካል ይህን የሚመለከት ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3/ የሚከተሉት ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች በመካከለኛ ሙቀት የማቃጠል ዘዴ አማካኝነት መወገድ የለባቸውም፡፡

ሀ. የታመቀ ጋዝ መያዣዎች፣

ለ. ከፍተኛ መጠን ያለው ሪአክቲቭ ኬሚካል፣



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment Forest & Climate Change Record & Archive Commission

ሐ. ሀሎጂኔትድ የእንስሳት መድኃኒት፣

መ. እንደ ፒቪሲ ያሉ ሀሎጂኔትድ የፕላስቲክ መያዣዎች፣

ሠ. ከፍተኛ የሜርኩሪ ወይም የካድምየም መጠን ያላቸው ለምሳሌ፡- የተሰበሩ ቴርሞሜትሮች፣ ያገለገሉ ባትሪዎች እና የሊድ ጠርዝ ያላቸው የእንጨት ፓናሎች፣

ረ. የታሸጉ ወይም ከፍተኛ የብረት ይዘት ያላቸው አምፒዩልስ፣

4/ የመጨረሻው አመድ ክፍት ቦታ ላይ መጣል ወይም መበተን የለበትም፡፡ ተሰብስቦ አግባብ ያለው አካል በመረጣው ላይ በተሳተፈበት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መወገድ አለበት፡፡

8. **ባለ ከፍተኛ ሙቀት ማቃጠያ** (High-Temperature Incineration)

1/ ባለ ከፍተኛ ሙቀት ማቃጠያ ምድጃዎች ባለጥንድ ክፍል ወይም ፓይሮሊቲክ ሆኖ የማቃጠያ ኃይሉ ከ1200 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ በሆነ ሙቀት የሚሰራ እና የመቃጠያ ጊዜው በሁለተኛዉ ክፍል ዉስጥ ቢያንስ 2 ሴኮንድ መሆን አለበት፡፡

2/ ባለ ከፍተኛ ሙቀት ማቃጠያዎች የጋዝ ማጽጃ መሳሪያ ሊገጠምላቸው ይገባል፡፡

3/ ማቃጠያዎቹ በሚመለከተው አካል ልኬታቸው መፈተሽ ያለበት ሲሆን አግባብ ባለዉ አካል ሲጠየቁ የምስክር ወረቀት መቅረብ አለበት፡፡

4/ የእንስሳት ጤና ተቋማት እና አስወጋጅ ድርጅቶች ሃሎጂኔትድ ምርቶችን ለማቃጠል የሲሚንቶ ማምረቻ ላይ የተገጠመን ማቃጠያ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

5/ በአንድ ጊዜ ወደማቃጠያዉ መግባት ያለበት ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ከጠቅላላ ማቀጣጠያ መጠን አነስተኛ ድርሻ ያለዉ ወይም ከ5 በመቶ ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

6/ የማቀጣጠያ ክፍሎች መዘጋት እንዳያጋጥም የእንስሳት መድኃኒት ማሸጊያዎችን መፍታት እና/ወይም መፍጨት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

7/ ሀሎጂኔትድ ንጥረ ነገሮች እናፖቫይደን አይዎዲን በከፍተኛ ማቃጠያ አማካይነት ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

8/ የመጨረሻው አመድ ክፍት ቦታ መጣል ወይም መበተን የለበትም፡፡ ተሰብቦ አግባብ ያለዉ አካል በመረጣው ላይ በተሳተፈበት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መወገድ አለበት፡፡



የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment,Forest & Climate Change
Record & Archive Commission

## ዕዝል 2
## የእንስሳት መድኃኒት ቆሻሻ መመዝገቢያ መዝገብ

| | የእንስሳት መድሃኒት ምርቶች ቆሻሻ ዝርዝር (የሳይንሳዊ ስም እና የንግድ ስም፣ ጥንካሬ እና የመድሃኒቱ ተፈጥሯዊ ይዘት) | የመለኪያ አይነትና መጠን | ብዛት | የባች ቁ | የተመረተበት እና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን | የሚወገድበት ምክንያት (የአገልግሎቱ ጊዜ ያበቃ፣ የተጎዳ፣ ከማሸጊያው የፈሰሰ ወዘተ) | አምራች/ አቅራቢ | መጋዘኑ የሚገኝበት ቦታ | የግገር ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | | |
| 3. | | | | | | | | | |
| 4. | | | | | | | | | |
| 5. | | | | | | | | | |
| 6. | | | | | | | | | |
| 7. | | | | | | | | | |
| 8. | | | | | | | | | |
| 9. | | | | | | | | | |

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር
Environment, Forest & Climate Change Commission Record & Archive

## ዕዝል 3፡ ለእንስሳት ጤና ተቋማት የሚሰጥ የእንስሳት መድኃኒት ማስወገጃ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

<table>
<tr><td colspan="6"></td><td colspan="4">የሚመለከተው የመንግስት አካል ስም<br>ምርቱ የሚወገድበት ቀን</td></tr>
<tr><td colspan="10">እኛ ከታች ፊርማችን የሰፈረው (የምርት አስወጋጅ ድርጅቱ ስም) ……………. የሆነው ድርጅት የምርት የማስወገድ ፈቃድ ቁ. ……………. እና አድራሻቸው …………….. የሆነው ድርጅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የእንስሳት መድሃኒት የሆነ ……………. ማስወገዱን እናረጋግጣለን፡፡</td></tr>
<tr><td></td><td>የእንስሳት መድሃኒት ምርቶች ቆሻሻ ዝርዝር (የሳይንሳዊ ስም እና የንግድ ስም፣ ጥንካሬ እና የመድሃኒቱ ተፈጥሯዊ ይዘት)</td><td>የመለኪያ አይነትና መጠን</td><td>ብዛት</td><td>የባች ቁ</td><td>አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን</td><td>የሚወገድበት ምክንያት (አገልግሎቱ ጊዜ ያበቃ፣ የተጎዳ፣ ከማሸጊያው የፈሰሰ ወዘተ)</td><td>አምራች/ አቅራቢ</td><td>መጋዘኑ የሚገኝበት ቦታ</td><td>የግዢ ቦታ</td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td colspan="5">የባለሙያ ስም እና ፊርማ</td><td colspan="5">የበላይ ሃላፊ ስም እና ፊርማ</td></tr>
</table>

* የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሪከርድና ማህደር * Environment Forest & Climate Change Record Archive Commission